# ምዕራፍ አሥር

# ዘለዓለማዊ ሕይወት (መዳን)

## የትምህርቱ ዓላማ

የዚህ ትምህርት ዓላማ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ሰዎች እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ ለማመልከት ነው።

ዳኑ የሚባሉ በሽተኞች ናቸው፤ ይኸውም በሽተኝነታቸው ማለትም ሽባነታቸው፣ ዕውርነታቸው፣ ጎብጦ መሄዳቸው፣ ለሰው የማይታየውም በውስጥ እነርሱን የሚሰማቸው የበሽታ ዘር ሲጠፉላቸው ዳኑ፣ ተፈወሱ፣ ጤነኛ ሆኑ ይባላሉ። ከላይ በነጠላ ሰረዝ እየለየን ያስቀመጥናቸው የደኅንነት ዘይቤዎች (ግሦች) የሚነገሩላቸው በሽተኞች ሁለት ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ።

1. ከጊዜ በኋላ ጤና ያጡ፣
2. ከእናታቸው ማኅፀን ጀምሮ ገና ሲፈጠሩ የአካልም ሆነ የአእምሮ ጉድለት ያለባቸው። (ዮሐ 9፥1-11)

ከጊዜ በኋላ ጤና ያጡ ሰዎች ዳኑ ሲባል የቀደመ ጤናቸውን አገኙ፣ ሕመማቸው ለቀቃቸው፣ እንደቀደመ ኑሮአቸው በሰላም በጤና መኖር ቻሉ ማለት ነው።

ከእናታቸው ማኅፀን ጀምሮ ሽባ፣ ዕውር፣ ዲዳ ወዘተ ሆነው የዚህን ከንቱ ዓለም ኑሮ የጀመሩት ደግሞ "ዳኑ" ሲባል ከእናታቸው ማኅፀን ጀምሮ ያጡትን አካል፣ አእምሮ፣ ጤና አገኙ በሙሉ ጤንነት መኖር ቻሉ ማለት ነው።



ይህ በዓለም የምንሰማው ከሥጋ ደዌ የመፈወስ ዜና ሊለወጥ፣ ዳነ የተባለው ሊታመም፣ ተነሣ የተባለው ተመልሶ ሊሞት ይችላል። አሁን ግን የምናጠናው ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወት (መዳን) ነው። የደኅንነቱም ዓይነት ከላይ በአንደኛ ተራ ቍጥር እንደተጠቀሰው የነበረንን ጤናችንን መልሶ የማግኘት መዳን ነው። የሰዎችን ነገረ - ሕይወት የሚያጠና ክርስቲያን ከምን? በማን? እንዴት? መቼ? ዳኑ ብሎ ለመጠየቅ በአንጻሩም ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት የሚከተሉትን ለጥናት ጋባዥ ጥያቄዎች መጠየቅና መልሳቸውን ማግኘት ይኖርበታል።

ጥያቄዎቹም፦

1. ሰው እንዴት ተፈጠረ?
2. ሰው ከተፈጠረ በኋላ እንዴት ይኖር ነበር?
3. ሰው ምን ሆነ?
4. ሰው ምን አገኘ?
5. የሰው መጨረሻው ምን ይሆናል? የሚሉት ናቸው።

## 1) ሰው እንዴት ተፈጠረ፤

1. ሰው በስድስተኛው ቀን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ከአምስተኛ ባሕርየ ነፍስ ግሩምና ድንቅ ሆኖ መንፈሳዊ ሕይወቱ፣ መንፈሳዊ አካሉ፣ ሥጋዊ አካሉ፣ የተስተካከለ ሆኖ ተፈጠረ። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት "አቤቱ ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ።" (መዝ 138፥14) ብሎ እንደተናገረው ሰው ሲፈጠር ግሩምና ድንቅ ሆኖ ተፈጥሮ ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያ ምዕራፍ አውጥተን ስለ ሥነፍጥረት ስናነብ፣ እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ "መልካም ነበር" ይላል። ስለሆነም እግዚአብሔር ከፈጠራቸው መልካም ፍጥረቶች መካከል ሰው አንዱ መሆኑ አያጠያይቅም (ዘፍ 1፥4) የመጀመሪያ ቀን ፍጥረት ቁ. 10-11፣ የሁለተኛው ቀን ፍጥረት፤ ቍ.

12-13 የሦስተኛ ቀን ፍጥረት ቍ.18 የአራተኛው ቀን ፍጥረት ቁ.21፣ የአምስተኛው ቀን ፍጥረት ቁ.25 የስድስተኛው ቀን ፍጥረት መልካም እንደነበረ ይናገራል።

ይልቁንም ቁ.31 ላይ ሰው ከተፈጠረ በኋላ "እጅግ መልካም ነበር" ይላል "እጅግ" የሚለው ሐረግ የተጨመረው ግሩምና ድንቅ የሆነው የፍጥረት ሁሉ ቁንጮ ሰው ስለተፈጠረ መሆኑ ግልጽ ነው። ፍጥረት ሁሉ ያለ ሰው መልካም ሲሆን ከሰው ጋር ደግሞ እጅግ መልካም ነበር።

## 2. በእግዚአብሔር መልክና ምሣሌ ተፈጠረ፣ ይህ ማለት፡-

ሀ. እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ገዥ እንደሆነ ሰውም የፍጥረታት ሁሉ ንጉሥ ሆኖ ተፈጠረ ማለት ነው። ይህንንም የምናረጋግጠው በዘፍ 1፥26-27 እና 2፥19 በተነገረው ቃለ እግዚአብሔር ነው። ም.2፥19-20 ያለው ቃለ እግዚአብሔር ሁለት ነገር ያስተምረናል።

1. ሰው ለእንስሳትና ለአራዊት ስም በማውጣቱ የተሰጠውን የቋንቋ ችሎታ፣
2. እግዚአብሔር ለፈጠራቸው ፍጥረታት ስም በማውጣቱ በላያቸው ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለው ጌታቸው መሆኑንና የበላይነቱን ያመለክታል (2ነገ 24፥17. ዳን 1፥6-7) ካለው ጋር አነጻጽር።

ለ. እግዚአብሔር ለባዊ፣ ነባቢ፣ ሕያው እንደሆነ፣ ሰውም ለባዊ ነባቢ ሕያው ሆኖ ተፈጠረ እግዚአብሔርን የማያመልኩ የሳይንስ ሊቃውንትም ሳይቀሩ አገናዛቢውን የእእምሮ ችሎታ ያገኙት ከእግዚአብሔር ነው። (ሮሜ 1፥18-19)



ሐ. እግዚአብሔር የወደደውን ማድረግ የሚችል ሕያው አምላክ እንደሆነ ሰውም ነጻነት ያለው ፍጡር ሆኖ ተፈጠረ። (ዘዳ 30፥19-20)

መ. ሰው ዘለዓለማዊ ሆኖ ተፈጠረ ይህም ማለት በእግዚአብሔር መንግሥት ጻድቃንም ሆኑ ኃጥአን እንደየሥራቸው ዋጋቸውን በመቀበል ነው።

ሠ. እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ (ዮሐ 4፥16) ሰው የመውደድና የመጥላት ችሎታ ያለው ሆኖ ተፈጠረ (ማር 12፥30)

3. ሰው ከእንስሳት በተለየ ሁኔታ ተፈጠረ። (ዘፍ 2፥7) እግዚአብሔር "እኔ ሕያው ነኝ" በሚልበት በሕይወት እስትንፋሱ ሕይወትን ሰጥቶ፣ ከደማውያን ፍጥረታት አክብሮና አልቆ ፈጠረው። (ዘዳ 32፥40, ኢዮ 33፥46)

4. በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረው ሰው የመንፈሳዊ መልኩ ባሕርያዊ መግለጫ በሆኑ እውነት፣ ጽድቅ፣ ፍቅር፣ ቅድስና፣ አምላኩን መሰለ። (ዮሐ 4፥24, ኤፌ 4፥24, ቈላ 3፥10)

5. ከመላእክት ሥጋ በመልበሱ ጥቂት ያነሰ፣ በክብር ግን የላቀ ያጌጠ ሆኖ ተፈጠረ። መላእክት እርሱን ለመርዳት ተፈጠሩለት (ዕብ 1፥14, መዝ 90፥11, ራዕይ 4፥10-11) በኋላ አምላክ ሰው ሲሆን ሰው አምላክ ሆኖ ይገዛቸዋል። (ኤፌ 1፥18-23, 2፥6-7, 1ቆሮ 6፥3)

6. ወንድና ሴት ሆኖ ተፈጠረ። (ዘፍ፡ 1፥26-28, 2፥18-19) ሴትን (ሔዋን) እግዚአብሔር ሲፈጥር እንደሱ (እንደ አዳም) ያለች በባሕርይ የምትመስለው የምትተካከለው አድርጎ ነው የፈጠራት። ምክንያቱም

ሰው ያለው ባሕርይ የእንስሳ ብቻ ሣይሆን ሕያው ፍጥረት ስለሆነ የእንስሳ ጓደኛ ስለማይሆነውና ስለማይስማማው ነው (ዘፍ 2፥20)

7. ሰው ደመ ነፍስ ሥጋ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ሕይወት ያለው ሆኖ ተፈጠረ። (1ተሰ 5፥23)

## 2) *ሰው ከተፈጠረ በኋላ እንዴት ይኖር ነበር፤*

እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ በዓለም ላይ በተሟላ ሁኔታ አክብሮ አስቀምጦት ነበር። ለምሳሌ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከብዙው በጥቂቱ ብንጠቅስ፤

1. የዕረፍት ቀን ተሠራለት፣ ለሰነፍ እረፍት የለውም፣ አዳም ግን በገነት ሲቀመጥ ያበጃት ይጠብቃት ዘንድ ነበር ስለዚህ ለመስተገብረ ምድር አዳም የዕረፍት ቀን ሠራለት (ዘፍ 2፥3)
2. አጥጋቢ ምግብ ቁ.9
3. ምቹ ቦታ ቁ.8-15
4. ተስማሚ ሥፍራ ቁ. 1
5. የሞራል ምርጫ ቁ. 9-17
6. ተገቢ ሥልጣን ቁ. 19-20
7. አስደሣች መሰል ጓደኛ (ባልንጀራ) ቁ. 21-25 ተዘጋጅቶለት ነበር።

ይህን በመሰለ ሁኔታ ይኖር ነበር በተጨማሪም ሕመም፣ ሞት፣ ኀዘን ዛሬ በዓለም የሰለጠኑት ሁሉ ሳይሰለጥኑበት ይኖር ነበር።

## 3) *ሰው ምን ሆነ?*

ተፈትኖ በኃጢአት ወደቀ



### 1. *ፈታኙ፤*

በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ውስጥ ክፉ የሚባል ነገር እንደሌለ፣ እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ “መልካም” እንደሆነ ተጽፏል። ወደ ም.2 ቁ.17 ስንሸጋገር “ክፉ” የሚል ቃል ይገጥመናል። ይህ ክፉ የሚለው ቃል ወደ ዓለም አዲስ ነገር መግባቱን ይነግረናል። “መልካምና ክፉ የምታሳውቀውን አትብላ” በማለት እግዚአብሔር በመጀመሪያ ባልነበረ ክፉ የሰው ልጅ ተጠምዶ እንዳይገኝ የመከረበት ክፍል ነው። ይህ ክፉ ከየት መጣ? ምዕራፍ ሁለት አይገልጽልንም በዓለም ክፉ መኖሩን ነው እንጂ ከየት እንደመጣ አይናገርም። በምዕራፍ ሦስትም ቢሆን ከዚህ የተሻለ መልስ አናገኝም ክፉው ማን እንደሆነ የታወቀው በሐዲስ ኪዳን ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ መተርጉማን ሊቃውንት (ኢሳ 14፥12-12, ሕዝ 28፥11-19) ያለውን ቃል እግዚአብሔር በመጥቀስ ስለክፉው አመጣጥና አወዳደቅ ይተረጉማሉ፣ ይተርካሉ። በአዲስ ኪዳን ግን በደንብ ታውቋል። (2ጴጥ 2፥4, ራዕይ 12፥6, ይሁዳ ቁ.9) ክፉውም ወደ ሰው የቀረበ በእባብ አድሮ ነው። ስሞቹም፦

1. በዕብራይስጥ ሠይጣን፣ ትርጉሙም መስሐቲ፣ ስሁት፣ የውሸት አባት ማለት ነው፣
2. በግሪክ ዲያብሎስ ትርጉሙ ከሳሽ (ዘካ 3፥1-5, ራዕይ 12፥10) ማለት ነው።

ከሳሽ ዲያብሎስ የእግዚአብሔርን ስም በሰዎች ፊት (ዘፍ 3፥4-5) የሰውን ስም በእግዚአብሔር ፊት ያጠፋል (ኢዮ 1፥6-12, 2፥1-6) ከሳሽ ዲያብሎስ ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ ኢየሱስን በመዋዕለ ጾሙ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ በማለት ስለልጅነቱ ጥርጥርን ከመዝራቱም በላይ ራሱን ተቆርቋሪ አባቱን ጨካኝ በማድረግ እንድትራብ እንድትጠማ የሚያደርግ አባትህ ልክ አይደለም የማለትን ያህል የፈዘዘ ድንጋይ ይዞ እርሱን ተቆርቋሪ በማድረግ አባቱን አማለት፤ እራሱን ግን አዛኝ አድርጎ

ድንጋዩን ኅብስት አድርግና ብላ በማለት እንደመጀመሪያው ሰው በምግብ ሊፈትነው ሊጥለውም ፈለገ። ኢየሱስ ግን አንተ ከሳሽ ከዚህ ወግድ (ጥፋ) አለው። (ሉቃ 4፥1-13, ማቴ 4፥1-10) ይመልከቱ።

## 2. አወዳደቁ፤

ፈታኙ ከመውደቁ አስቀድሞ በኢሳ 14፤, ሕዝ 28፥11-19 ላይ እንደተጠቀሰው ያለ ክብር ነበረው። እንዴት ከክብሩ እንደወደቀ በራእይ 12፥8-13 ከቅዱሳን መላእክት ጋር ተዋግቶ ድል በመነሣቱ ወድቋል። እግዚአብሔርም በእርሱና በሠራዊቶቹ ፈርዶባቸዋል፡ (2ጴጥ 2፥4-6)

## ፈታኙ ራሱን ወደሰው በምን ዓይነት ሁኔታ አቀረበ?

1. በእባብ አድሮ ወይም በእባብ ተመስሎ በለመዱት መልክ (ዘፍ.3፥1-10, ዘፍ 2፥19-29) ቀረበ ጥቅሶቹን ያገናዝቡ።

2. ራሱን ተቆርቋሪ በማድረግ፣ ደካማ ጐንን በመጠቀም አምላክ እንድትሆኑ በማለት (ዘፍ 3፥4) ሰው ሁሉም ያለው ስለነበር፣ ከኪሩቤል ላይ መቀመጥ አምላከ ሰማይ መሆን እንደሚችሉ ነገራቸው እነርሱም ተቀበሉት በፈተና ወደቁ።

3. ቃለ እግዚአብሔርን በማጣመም "በውኑ እግዚአብሔር የገነትን ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አገዟልን?" (ዘፍ 2፥1-2) አለ እግዚአብሔር ግን "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ" (ዘፍ 2፥17) ብሎ አዘዘው እንጂ የገነትን ዛፍ ሁሉ አትብሉ አላለም ነበር።

4. በመዋሸት፣ "ሞትን አትሞቱም" (ዘፍ 3፥4) አላቸው የሐሰት አባት ነውና (ዮሐ 8፥44) ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ (ዘፍ. 3፥8) መንፈሳዊ



ሞትን ወዲያውኑ ሥጋዊ ሞትን ደግሞ እንደ ሞቱ (ዘፍ 5፥5) ይነግረናል።

5. እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ በማለት በማስጎምጀት ማለትም የሥልጣን አምሮት ልባቸው ውስጥ በማስገባት (ዘፍ 3፥5)

6. በገነት ካሉት ለሕይወት ደስ ከሚያሰኙ ዕፅዋት ሁሉ የሞትን ዕፅ (ዛፍ) በማሳየት ፣ ለእግዚአብሔር ቃል ተቃራኒ የሆኑትን የሐሰት ቃላት በመደርደር ከአምላካቸው ለመለየት ቀረበ።

## የሰው ውድቀት፤

መጽሐፍ ቅዱስ "ሴቲቱም አየች" ይላል (ዘፍ 3፥6) ሰው በኃጢአት በወደቀበት ቀን ሰይጣን የሰነዘረው ፈተና መግቢያ በር ያገኘው በሴቲቱ ጆሮ በሹክሹክታ በሚሰማት ቃል ብቻ ሳይሆን በዓይኗም በኩል ጭምር ነው። በጆሮዋ ሰማች፣ በዓይኗም አየች፣ የተከለከለውም ዛፍ ለዓይን የሚያስጐመጅ ሆነላት። ለጥበብም መልካም እንደሆነ ተሰማት። ከእነዚህም ቃላት ስለኃጢአት ጠባይና ተንኮል አንድ ትምህርት ብንወስድ መልካም ነው። በፈተና ሰዓት ኃጢአት ለሰው ጥሩና አስደሳች የሆነውን ነገር የምትሰጥ አስመስላ ልብን ልትማርክ ትችላለች። ሰውም በዚህ ተንኮል ተታሎ የሚያስደስተኝን የሚጠቅመኝን ነገር ለምን አልፈልግም በማለት ኃጢአት የምታቀርበውን ነገር ለማግኘት ይሽቀዳደማል ሴቲቱም በተፈተነችበት ሰዓት እግዚአብሔር አምላክ ለማየት ደስ የሚያሰኙትን፣ ለመብላትም መልካም የሆኑትን ሌሎች ዛፎች ሁሉ ረስታ ያን የተከለከለውን አንዱን ብቻ ትኩር ብላ ተመለከተች ቆየችና የሚጠቅመኝ ይህ ብቻ ነው ሌላው አይሆነኝም በሚል ስሜት ተማርካ ምኞቷን ለመፈጸም ስትል ፍሬዋን ወስዳ በላች። ለባሏም ሰጠችው። የኃጢአት ፍሬ ለጊዜው አስደሣችና ጣፋጭ መስሎ ታየ ፍጻሜው ግን መራራ መሆኑ ወዲያው ለሰው ታወቀ።

## ከውድቀት በኋላ የተከሰተው አሳዛኝ ነገር፤

ሰው ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ ከመቅጽበት ተለወጠ።

1. በእግዚአብሔር ፊት ሐፍረት ተሰማው (ዘፍ፡ 3፥7)

2. በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው ኅብረት ተቃወሰ። ሰውም ከእግዚአብሔር ፊት ሸሸ። ቅጠል ውስጥ ተሸሸገ ቁ.8 ከጥፋት በኋላ ለሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ፊት መቅረብ የተሻለ መስሎ አልታየውም፤ ፈራ፣ ራደ፣ ተንቀጠቀጠ፣ ልቡ ተጥፋፋበትና ሣሩን፣ ቅጠሉን፣ ዛፉን ተራራውን ከእግዚአብሔር ቁጣ መደበቂያ ለማድረግ ከንቱ ሙከራ አደረገ ላያድኑት ላይጠብቁት ፍጥረታትን ተማጸነ (ዘፍ.7፥10, ራዕይ 6፥16, ሉቃ.23፥30)

3. ካለመታዘዙ የተነሣ በኅሊና ወቀሳ የሚጨነቅ ሆነ (ቁ.81, 1ዮሐ3፥20-22, ዮሐ16፥8)

4. በሰውና በሰው መካከል የነበረው አንድነት ፈረሰ አንደኛው ራሱን ጻድቅ ለማድረግ ሲል ሌላውን ጥፋተኛ አድርጎ ማቅረብ ግድ ሆነበት። አዳም በበኩሉ ራሱን ነጻ ለማድረግ ሲል ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ በማለት ባልንጀራውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ጭምር በጥፋተኛነት አቀረበ (ዘፍ 3፥12) በአነጋገሩ እግዚአብሔር ነጻ አይሆንም ምክንያቱም ወደ ስሕተት የመራችውን ሴት ፈጥሮ የሰጠው እርሱ ነውና። ሔዋንም በበኩሏ በእባብ አመካኘች (ቁ.13) ሁሉም ራሳቸውን ነጻ ለማድረግ ሞከሩ። ነገር ግን ሰው ልዩ ልዩ ምክንያት ቢፈጥርም ከሠራው ሥራ ኃላፊነት ሊያመልጥ አይችልም እግዚአብሔር በሠራው ኃጢአት የሚጠይቀው ኃጢአተኛውን ነውና።



5. ሥቃይ፣ ጭንቀት፣ ሽብር . . . ኃጢአትን ተከትለው መጡ (ቁ.16፤)፣ በሰው በደል ምክንያት ምድር ሁሉ ከእርግማን በታች ወደቀች፤ ከሰው ውድቀት በፊት በኤደን ገነት ሰፍኖ የነበረው ሰፊ ሰላም ከምድረ ገጽ ጠፋ። (ቁ. 17-18)

6. "በበላህ ቀን ትሞታለህ" በተባለው መሠረት ሁለት ሞት ሞተ። አንድ ወዲያውኑ መንፈሳዊ ሞት ሞተ (ዘፍ፡ 3፥8, ሕዝ 18፥4, ኤፌ 2፥1-5) በኋላም በ930 ዓመት ከእግዚአብሔር የተለየች (የሞተች) ነፍስ ከሥጋዋ በመለየት እርሷ ወደ ሲኦል ሥጋም ወደመቃብር ወረደ (ዘፍ 5፥5) ድካም የሞላበት የሰው ምድራዊ ጉዞ ካለፈ በኋላ ሰውነት ገሎ ይወድቃል በመሬትም ጉድጓድ ተከፍቶለት በአፈር ተሸፍኖ ይተኛል ሰው ከአፈር የተወሰደ አፈር ነበር። ወደ አፈርም ይመለሳል (ዘፍ 3፥19) እነሆ ይህ ነው ለማይባል ክብር የተጠራው ሰው በራሱ ክፉ ሥራ ምክንያት እስከዚህ ድረስ ውርደትና ሐዘን ደርሶበታል።

በሕይወት የተፈጠረ ሰው ለሞት ተገዥ ሆነ በመሞቱም የእንስሳት ጓደኛ ተባለ በረጋፊ የዱር አበባም ተመሰለ (መዝ 102፥15-16) የኃጢአት ደመወዝን ወሰደ (ሮሜ 6፥23) እድሜውም አጭር ሆነ (መዝ 89፥8-10)

7. የዚህ ዓለም ገዥ ሰው ራሱን ለሰይጣን ከማስገዛቱም በላይ የሚገዛውን ዓለም ይዞ በሰይጣን ቊጥጥር ሥር በመዋሉ ዓለማችን ከጌታዋ ጋር ለሠይጣን ተገዥ ሆነች ስለሆነችም ሠይጣን የዚህ ዓለም ገዥ ለመባል በቃ (ዮሐ 12፥3-12, ቆሮ 4፥4)

8. እግዚአብሔርን መስሎ የተፈጠረ ሰው በኃጢአት በመውደቁ፣ የሠይጣንን ሐሳብ በመቀበሉ ሠይጣንን መሰለ፤ ዘር በምድር ላይ የሚተካበት ጊዜም የመጀመሪያውን ነፍሰ ገዳይና ድንጋይ ወርዋሪ

ቃየልን በመጀመሪያው ነፍሰ ገዳዩ በዲያብሎስ አምሳል (ዮሐ 8፥44-46) እንዲሁም መንፈሳዊ ምውት በሆነው አምሳያው መንፈሳዊው ምውት ሴት ተወለደ ከመራራ ውስጥ ጣፋጭን ነገር፣ ከርኩስ ቅድስና ማፍለቅ አይቻልምና (ኢዮ 14፥4, መዝ 50፥5, መዝ 57፥3-4)

9. የአዳምና የሔዋን ልጆች ሁሉ በእነርሱ አማካይነት የሠይጣን ተገዥዎች በመሆናችን የእውሬውን (የዲያብሎስን) ምክር ሰምተን የእግዚአብሔርን ቃል በመጣላችን የእግዚአብሔር ልጆች በመባል ፈንታ የእባብ የአራዊት የዲያብሎስ ልጆች "ትውልደ አራዊተ ምድር" የእባብ የእፉኝት ልጆት ለመባል በቃን (ማቴ3፥6, ማቴ 12፥34, ሉቃ 3፥7) መድኃኒታችንም በግልጽ ሰዎችን "አትሙስ እምአቡክሙ ሰይጣን አንትሙ" በማለት የዮሐንስን ሐሳብ አጸደቀ (ዮሐ 8፥44)።

10. ዕርቃናቸውንና አሳዛኙን ነገር ለማየት ዓይናቸው ተገለጠ። (ዘፍ 3፥7)
11. ከገነት ተባረሩ በሩም በእሳት ሰይፍ ተዘጋባቸው። (ቁ.23-24)
12. ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ የገጠመውን የተቃወሰ ሕይወት ቅ/ጳውሎስ በሮሜ 7፥13-25 እንደሚከተለው ገልጾታል።
   ሀ) በጎ የሆነው ነገር ሞት ሆነበት (ቁ.13)
   ለ) ከኃጢአት በታች ሊሆን የተሸጠ የሥጋ ሰው ሆነ (ቁ. 14)
   ሐ) የሚያደርገውን የማያውቅ፣ የሚጠላውን የሚያደርግ፣ የሚወደውን የማያደርግ ሆነ (ቁ.15)
   መ) የሚያደርገውን ሁሉ በሱ ያደረ ኃጢአት የሚያደርገው በሥጋው በጎ ነገር የሌለው ሆነ (ቁ.17-20)
   ሠ) በእግዚአብሔር ሕግ ደስ እንኳ ቢለው የኃጢአት ምርኮኛ ሆነ (ቁ. 23)
   ረ) በመጨረሻም ትግሉ ፣ ጽድቁ፣ ራሱን ለማዳን የሚያርገው ሁሉ የመርገም ጨርቅ ቢሆንበት (ኢሳ 64፥6) እንዲህ ብሎ ጮኸ "እኔ



ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ፣ ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?" (ሮሜ 7፥24-25) ማን ያድነው ይሆን?

**ጥቅስ በግዕዝ**

"ወድቀ ሰብእ በእንተ ኃጢአቱ ወተሰደደ እምገነት በእንተ ኢሰሚዕ፤ በጽሐነ መፍቀሬ ሰብእ እስመ ይጸርሑ ነቢያት እንዘ ይብሉ አኮ ተንባል ወአኮ መልአክ አላ ውእቱ እግዚአብሔር ይመጽእ ወያድኅነነ ወዳዊትሂ ያስተበፅዑ እንዘ ይብል ዘይርዕዮሙ ለእስራኤል አዕምዕ ወይርእዮሙ ለአባግዓ ዮሴፍ ዘይነብር ላዕለ ኪሩቤል አስተርአየ አንሥእ ኀይለከ ወነአ አድኅነነ፤"

**ትርጉም፡-**

"ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ባለመስማቱ ምክንያት ከገነት በኃጢአቱ ተባረረ ሰው ወዳጅ ጌታም ደረሰልን፣ ነቢያት በመልአክ በአስታራቂ ሳይሆን እሱ ሰው ሆኖ ያድነናል እያሉ ሲጮሁ ዳዊትም በበኩሉ እስራኤልን የምትጠብቅ አድምጥ እንደ ዮሴፍ በጎችም የምትመለከታቸው እያለ ማለደ በኪሩቤል ላይ የሚቀመጠው በሥጋ ማርያም ታየ ኀይልህን አንሣ መጥተህም አድነን ብሎም ተነበየ" እንዳለ መጽሐፈ ቄርሎስ።

## የድኅነት ተስፋ

ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ቢጥልም እግዚአብሔር ግን ሰውን እስከ መጨረሻው ፈርዶ በመከራ ውስጥ ሊጥለው አልፈለገም። በመሆኑም ቅዱስ እንደመሆኑ አስቀድሞ እንደተናገረው በሰው ላይ ጊዜያዊ ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ ቢፈርድበትም (ዘፍ 3፥17-24) የምህረት ጌታ የተስፋ ቃሉን አሰማው፤ ያሰማውም

1. ራሱ በቃሉ፣
2. በነቢያት አድሮ ነው።

# እግዚአብሔር የሰጠው የመጀመሪያ የተስፋ ቃል

"በአንተና በሴቲቱ፣ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትነክሳለህ።" የሚል ነበር (ዘፍ 3÷15-16) ሰው በኃጢአቱ ራሱን በወረወረበት ጨለማ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ደኅንነትን የሚያበሥር የብርሃን ጮራ የታየው ይህንን የተስፋ ቃል በሰማበት ዕለት ነው። ከዚህ የተነሣ ብዙ ሰዎች ከፍ ብለን የጠቀስነውን ጥቅስ የመጀመሪያ ወንጌል እያሉ ይጠሩታል አባባላቸውም ልክ ነው። ምክንያቱም ሰውን ከወድቀት ያደረሰው ሰይጣን ድል እንደሚመታ በትንቢት መልክ የሚገልጥ በመሆኑ ነው። በአዲስ ኪዳን የሴቲቱ ዘር ክርስቶስ መሆኑን እናያለን። እርሱም ከዲያብሎስ ጋር ታገለ፤ አሸንፎም ራሱን ቀጠቀጠ፤ በመስቀል ላይ የሴቲቱ ዘር በልማደኛው ጠላት ሰኮናው ተነከሰ (ቈላ 2÷15) በመጀመሪያ አዳም የሞቱትን ሁሉ ሕያዋን አደረጋቸው። (1ኛ ቆሮ 15÷22)

ሁለተኛው የእግዚአብሔር ተስፋ "በዘርህ የምድር አሕዛብ ይባረካሉ" በማለት የሴቲቱ ዘር የተባለው በሴት በኩል አልፎ የአብርሃምን ዘር ተከትሎ የሚበቅል በጠላት ዲያብሎስ ምክንያት የመጣውን መርገም (ዘፍ 3÷13-20) ወደበረከት የሚለውጥ ዘር እንደሚሆን ተናገረ። እንዲሁም "እም ይስሐቅ ይሰመይ ለከ ዘርዕ" በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል (ዘፍ 21÷13) በማለት ተስፋውን ተናግሯል። አገናዛቢ ጥቅሶች (3÷14-29, 5÷6-32, 10÷21, 11÷10-16, 22÷18-20, ዘዳ 32÷7) ወደ ዳዊትም ስንመለከት ፍጻሜ የሌለውን ሠላም የሚያመጣ ዘር ከዳዊት ዘር እንደሚነሣ ተናገረ። (2ሳሙ 7÷12-13, ኢሳ 9÷6-7, ኤር 23÷5-6) በመጨመር ያገናዝቡ። በተጨማሪ ሊቃውንት (ዘፍ3÷9-10 እና ቁ.22-23) ያለውን ቃል እግዚአብሔር በመጥቀስ የወደፊቱን ተስፋ እንደሚያመለክት ይተረጉማሉ።



# እግዚአብሔር በነቢያት ያናገረው የተስፋ ቃል፤

1. ከድንግል እንደሚወለድ፣ (ኢሳ 7÷14, ማቴ 1÷23)
2. በቤተልሔም እንደሚወለድ፣ (ሚክ 5÷2, ማቴ 2÷5)
3. ቀዳማዊ አዳምን ወደቀደመ ቦታው ለመመለስ ወደ ግብጽ እንደሚሰደድ፣ (ሆሴዕ 11÷1, ማቴ 2÷14)
4. በናዝሬት እንደሚያድግ፣ (ማቴ 2÷23)
5. በጨለማ የሚኖሩ በእርሱ ብርሃን እንደሚያዩ፣ (ኢሳ 9÷1-2, ማቴ 4÷16)
6. በኃጢአት እሳት የሚገረፉትን ሁሉ እንደሚምር፣ (ኢሳ 42÷1-4, ማቴ 12÷18)
7. ሰዎች ቃሉን መስማት እንደማይችሉ ልባቸው እንደሚደነድን፣ (ኢሳ 6÷9-10, ማቴ 13÷14, ኢሳ 29÷13, ማቴ 15÷8-9)
8. በምሣሌ እንደሚያስተምር፣ (መዝ 77÷2, ማቴ 13÷34-35)
9. መምህረ ትሕትና ሆኖ በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ ኢየሩሳሌም እንደሚገባ፣ (ዘካ 9÷9, ማቴ 21÷5)
10. ምሁራን ነን ባዮች እንደሚንቁት፣ ነገር ግን የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ ሰዎችን እንደሚሰበስብ፣ (መዝ 117÷23-25, ኢሳ 8÷1, 14-15፤ ዳን 2÷34-35, ማቴ 21÷42)
11. የሚወለደው እግዚአ ዳዊት፣ አምላከ ዳዊት እንደሆነ በጠላቱ ራስ ላይ እንደሚቆም (መዝ 109÷1, ማቴ 22÷44)
12. በሠላሳ ብር እንደሚሸጥ፣ (ተረፈ ኤርምያስ 7÷6, ዘካ 11÷13, ማቴ 27÷9)
13. ለድሆች ወንጌልን፣ ለታሠሩ መፈታትን፣ ለዕውሮች ማየትን፣ ለተጠቁ ነጻነትን. . . . ለመስበክ እንደሚመጣ (ኢሳ 61÷1-12, ሉቃ 4÷17-21)

14. በአይሁድ ጉባዔ ተፈርዶበት እጆቹ፣ እግሮቹ ተቸንክረው መሰቀሉን፣ መራራ ሐሞት መጠጣቱን፣ ልብሱን ወታደሮች መከፋፈላቸውን፣ (መዝ 21፥11-24, ዮሐ 19፥23-24, 29-30)
15. መልክና ደምግባቱ እስኪጠፋ መሰቃየቱን፣ ስለእኛ መቁሰሉን፣ በመከራው መታገሱን፣ አለመዛቱን፣ መቃብሩ ከክፉ አድራጊዎች ጋር መሆኑን፣ ስለክፉዎች መማለዱን ወዘተ . . . (ኢሳ 53፥1-12, 1ኛ ጴጥ 2፥21-25)
16. ከሙታን መነሣቱን፣ (መዝ 77፥75, ማቴ 28)
17. ወደሰማይ ማረጉን፣ (መዝ 46፥5,ማር 16)
18. ዳግም መምጣቱን፣ (መዝ 49፥2, የሐዋ 1፥11)

## 1. *የሰው ደኅንነት ለምን በሕግ በኩል አልተፈጸመም?*

1.1 ሰው ከሥጋ የተነሣ ስለደከመ ሕግን መፈጸም ስላልቻለ፣ (ሮሜ 8፥3)

1.2 ሕጉም ሰውን ሊያግዘው ስላልቻለ፣ (ሮሜ 8፥4)

1.3 በመሆኑም ሰው በሕግ በኩል መዳኑ የማይሳካ ሆነ (ሮሜ 3፥20, ገላ 2፥16)

1.4 ሕግ መቅሰፍትን ስላስከተለ፣ (ሮሜ 4፥15) በመሆኑም በሕግ ያለው ጽድቅ ሳይሆንለት ቀረ፣ (ፊል 39፥10) ሰው የብሉይ ኪዳንን ሕግ መጠበቅ ባለመቻሉ ሕግንም ካልፈጸመ ስለማይጸድቅ አሁን የሚያስፈልገው ከሕግ በላይ የሚያደርገው ነው። ስለዚህ የሰው ልጅ በክርስቶስ መገለጥ በሕግ በኩል ለእርሱ ያልተቻለው በመሢሕ መገለጥና ለሕግ ታዛዥ ብቻ ሳይሆን ፈጻሜ ሕግ በመሆኑ የሚከተሉትን አገኘ።

ከሕግ በላይ ሆነ (ሮሜ 6፥14-15)፣ ያም የሆነው ሕግ ወደ ክርስቶስ መርቶ ስላደረሰው ነው (ገላ 3፥23-25)። ይህ ሲባል ግን ክርስቲያን ከብሉይ



ኪዳን ሕግ በላይ ሆነ ማለት ነው እንጂ ከክርስቶስ ሕግ በላይ ሆነ ማለት አይደለም። (ሮሜ 8፥3-6) የሰው ልጅ ከብሉይ ኪዳን ሕግ በላይ የሆነው ሰው ለዘመናት ሲሸራቸው የኖሩትን ሕግጋት ኢየሱስ በመፈጸሙ ነው (ማቴ 5፥17)። ሕጉንም የፈጸመው ለሕግ በመታዘዝ (ገላ 4፥4, 1ኛ ጴጥ 2፥22-23) የሕግን ቅጣት ስለሌሎች በመቀበል (ገላ 3፥10, ገላ 3፥10-13) የብሉይ ኪዳንን መሥዋዕት በራሱ በመተካት ነው (ዕብ 9፥1-14) ሰዎች ከብሉይ ኪዳን ሕግ በታች ነበሩ (1ኛ ቆሮ 9፥20, ገላ 3፥23) በክርስቶስ መልዕልተ ሕግ ተባሉ (ሆኑ) የሰው ልጅ ሕግን መፈጸም እያማረው በጎው ነገር ሞት ሆኖበት ለዘመናት ሲኖር (ሮሜ 7፥22, መዝ 39፥8) የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ሰው ሆኖ የልቡን አደረሰለት። በክርስቶስም መልዕልተ ሕግ ሆነ።

## 2. *በፍጡራን ለምን አልተፈጸመም*

2.1 በሰዎች መሥዋዕትነት፣ ሰዎች ሁሉ የአዳምን እና የሔዋን ልጆች በመሆናቸው ሁሉም ስለበደሉ (ሮሜ 3፥11-18) የሰው ጽድቅ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስላልኖረው (ኢሳ 64፥6)፣ ሰው ሰውን ለማዳን ስለማይችል (መዝ 48፥6-9)

2.2 ዓለምና በዓለም ያለው ሁሉ የሰውን የኃጢአት ዋጋ ሊመዝን ስለማይችል፣ የሰውንም ያህል ዋጋ ሊመዝን ስለማይችል (ማር.9፥36-37)

2.3 በኦሪት ሥርዓት ይቀርቡ በነበሩ መሥዋዕቶች የአማናዊ መሥዋዕት ምሳሌ ከመሆን ጋር ለቀድሶተ ሥጋ በማገልገል ረዱ እንጂ ዘለዓለማዊ የነፍስ መንጻትን መቀደስን አላመጡም (ዕብ 9፥8-14, 10፥1-10)፣

2.4 በቅዱሳን መላእክት በኩል ለምን አልተፈጸመም? ለሰው ሥጋና ደም ተለዋጭ የሚሆን ሥጋና ደም ስለሌላቸው (ዕብ 2÷14-16) ምክንያቱም የሰውን ሁለንተና ሥጋና ነፍስ ገንዘብ ያላደረገ አዳኝ ሊሆን ስለማይችል ነው (ዕብ 2÷14-16)።

ጥቅስ፡- እስመ በእንተ አዳም ለኵልነ ረሰየነ ኀጥአነ ወአግብርተ አጥረየነ ዲያብሎስ ማኅተመነ እንዘ ይጸውር ወክርታሲሁ ረሰየ ሕማመ ሥጋነ ወይቀውም እኩይ ፍልስጣ ጸሐፊ ወተምያን እንዘ ያርኢ መጽሐፈ ዕዳነ ወይትፈደየነ በሞትነ እምገዘኬ ኵሉ፣ መፍትው ይዕዜሂ ለኵልነ ይትፈደየን ዘእምቅስትነ እስመ ኵሉ አበሰ አሐዱ ዘከማሁ እግዚእነ ይትወሃብ ለቤዛነ እስመ ሎቱ ጽድቅ አድህኖ ውበእሲሰ ትሑት አድህኖ እምኢክህለ እስመ ውእቱሂ ይፈዲ ምስሌነ እዳ። ወመልአክሂ እምኢክህለ ተሣይጦትነ እስመ አልቦ ቤዛ ሥጋ በዘይትቤዘወነ፤ መፍትውኬ ዘአልቦ ኃጢአት ይሙት በሥጋሁ በእንተ ኃጢአትነ እስመ ዛቲመ ምክንያት ይእቲ እንተ ታድኅነነ በእንቲአሁ ...ትሑትኬ ብዕሲ እምኢክህለ አድኅኖ እስመ ትሑት ውእቱ ይፈቅድ ዘያድኅኖ በከመ ይቤ ጳውሎስ ኵልነ አበስነ ወአበሳነ ያቀርበነ ለዲያብሎስ ወዲያብሎስ ይፌንወነ ለሞት ውስተ ዓቢይ ሕማም ኮነ ትውልደ ሰብእ ወአልቦ ዘይባልሀ ወእለሰ ተፈነው ዓቀበተ ሥራይ ነቢያት ሥዕነ አሕይዎ። ወሶበ ርእዩ ከመ እምኩሉ ኪን ዘሰብእ አዐበ ቍስለ እገሪሆሙ ይጼውኡ ዓቃቤ ሥራይ ዘእምሰማይ ቦ ዘይቤ እግዚኦ አፅንን ሰማያተ ወረድ፣ ወቦ ዘይቤ አሕይወኒ እግዚኦ ወአሐዩ፣ ወቦ ዘይቤ አንሥእ ኃይለከ ወነዐ አድኅነነ፣ ወቦ ዘይቤ የኀድር እግዚአብሔር ምስለ ሰብእ፣ ወቦ ዘይቤ ፍጡነ ይረክበነ ምሕረትከ እግዚኦ፣ ወቦ ዘይቤ ዓሌ ሊተ እስመ ኃልቀ ኄር እምድር፣ ወቦ ዘይቤ እግዚኦ ነጽር ውስተ ረድኦትየ እግዚኦ አፍጥን ረዲኦትየ ዘሀሎ ይምጻእ ኅቤየ ወኢይጎንዲ ወቦ ዘይቤ ተረሣዕኩ ከመበግዕ ዘተገድፈ ሕሥሥ ለገብርከ ወበእንተ ዝንቱ ኢተሐየያ ለፍጥረት እንዘ ትትገፋዕ፣ ዘበአማን ንጉሥ ዘበሕላዌሁ አላ



መጽአ ዘሀሎ ወትረ ወወሀበ ቤዛ ዚአሁ" እንዳለ ጵርስቅሎስ ጳጳስ ዘሀገረ ቆገዐሞስ።

<u>ትርጉም፡-</u> በአዳም ኃጢአት ምክንያት ሁላችንንም ኃጥአን አደረገን ዲያብሎስ አሽከሮቹ አደረገን የአሽከርነት የባርነት ገዛና የያዘ የዕዳ ደብዳቤአችን ይዞ መከራ ሥጋ አጸናብን ክፉ ፍልስጣ የሚባል ጋኔን የሰውን ኃጢአት የሚጽፍ ተንኮለኛ የዕዳ ደብዳቤያችንን እያሳየ በሞት ፍዳችን ይከፈለናል።

ስለዚህ ሁላችንም በደለኞች ስለሆን ከባላንጋራችን (ከነፍሳችን ጠብ) ያድነን ዘንድ ይገባል በአንዱ በደለኞች እንደሆን እንዲሁ አንዱ ጌታ መድኃኒታችን ቤዛ ይሁንልን በእውነት ማዳን የሚቻለው እሱ ነውና።

ሰው ማዳን አይቻለውም አብሮ ከእኛ ጋር ዕዳ ከፋይ ስለሆነ መልአክም ከኃጢአታችን በመዋጀት ሊያድነን አይችልም ለሥጋችን ቤዛ የሚሆን ሥጋ በተፈጥሮው ስለሌለው፣ በመሆኑም ኃጢአት የሌለበት ጌታ በለበሰው ሥጋ ስለኃጢአታችን ሊሞትልን ቤዛ ሊሆነን ይገባል፣ እኛን ማዳን የምትችለው ምክንያት የደኅንነታችን መሠረት መሞቱ ናትና ስለእሱ ሞት ዋጋ እኛ ስለምንድን (ኢሳ 53÷1-12)

ደካማ ሰው ራሱን ማዳን ባልተቻለውም ነበር ደካማ ስለሆነ የሚያድነው ያሻዋል ቅ/ጳውሎስ "ሁላችን በደለኞች ነን" እንዳለ (ሮሜ 3÷23) በደላችንም ወደዲያብሎስ ያቀርበናል፤ ዲያብሎስም ወደ ሞት ይልከናል፤ የሰው ልጅ በጽኑ መከራ ውስጥ ወደቀ የሚያድነውም አልነበረም። ባለመድኃኒት ሆነው የተላኩት ነቢያትም ድኅነተ ነፍስን ማምጣት (ማድረግ) አቃታቸው ቁስለ ነፍሳችን፣ ሥጋችን ከሰው ጥበብ በላይ እንደሆነ ባዩ ጊዜ በሰማይ የሚኖረውን ባለመድኃኒቱን አሰምተው

በጸሎት በትንቢት ጠሩት "ኃይልህን አንሥተህ ና አድነን" ያለ አለ (ዳዊት ነው) በተስፋም "እግዚአብሔር ሥጋ በመልበስ ከሰዎች ጋር ያድራል" ያለም አለ "ሰማይን አዘንብለህ ውረድ" ያለም አለ "ቸር ሰው አልቋልና ወዮልኝ አቤቱ አድነኝ" (መዝ 11÷1) በማለት በምሬትም የተናገረ አለ "አቤቱ እኔን ለመርዳት ተመልከት እኔን ለመርዳትም ፍጠን" ያለም አለ "ወደ እኔ ለቤዛ የሚመጣው አይዘገይም" ያለም አለ (ኢዮብ ነው።)

"እንደጠፋ በግ ተረግሁ ባሪያህን ፈልገው" ያለም አለ (ዳዊት ነው) ስለዚህ በዲያብሎስ ስትገፋ ፍጥረትን ቸል አላላትም በአንዋዋሩ እውነተኛ የሆነው ንጉሥ ዘወትር የሚኖር እርሱ የእሱ የሆነውን ቤዛ ሰጠን።

## 4) *ሰው ምን አገኘ?*

*ጥቅስ በግዕዝ*

"ወአልብነ ምንትኒ ግሙራ ዘይክል ያቅርበነ ለአቂበ ሀብተ፡ ኢኪዳን ወኢመሥዋዕት ወኢያንሥእ ለነ ሊቀ ካህናት እምነ መላእክት ወኢእምነ ኃይላት እለ ይቀውሙ ቅድመ መንበሩ አላ አሐዱ ለሊሁ ወረደ ወተሠገወ እምህላዌነ ወኮነነ ሊቀ ካህናት ወአዕረገ ሥጋሁ በእንቲአነ መሥዋዕተ ለአቡሁ ወአብጽሐነ ሎቱ፡ በዘቦቱ፡ ሐመ"

*ትርጉም፡-*

"ኪዳንም ቢሆን መሥዋዕትም ቢሆን ወደእሱ ሊያቀርበን የቻለ አንዳች ነገር አልነበረም በመንበሩ ዙሪያ ከሚያመሰግኑት ኃይላትም ሆነ ሊቃነ መላእክት ወገን ሊቀ ካህናት አልሾመልንም አንዱ ራሱ ወርዶ የሰውን ባህርይ ነሥቶ ሥጋን ነሥቶ (ለብሶ) ስለእኛም በታመመ ገንዘብ ገንዘቦቹ፡ አደረገን" (ዮሐንስ አፈወርቅ ሃ.አበው)



# የእግዚአብሔርን ልጅ አገኘ

## የአዳኙ የእግዚአብሔር ልጅ መገለጥ፤

- ሰው እኔን ራሴን ማዳን ስላልሆነልኝ "እጅህን ከአርያም ላክ አድነኝም" (መዝ 143÷7) አለ።
- በጽድቁ በቅድስናው ወደ እግዚአብሔር ዙፋን መድረስ መቀደስ ቢያቅተው "ብርሃንህንና እውነትህን ልከህ ወደቅድስና ተራራህና ወደማደሪያህ ይውሰዱኝ" (መዝ 42÷3)
- ጽድቁ ቢበከልበት ዋጋ የለሽ ቢሆንበት "አንተ ጽድቅ ሁንልኝ" (ኤር 23÷6) ወዘተ እያለ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። እግዚአብሔርም የሰውን ጩኸት ሰምቶ ወደዓለማችን ቢመለከት አንድም ጻድቅ (ጽድቅ) አልነበረም። ፍርድም አልነበረም። ወደ እርሱም ማልዶ ሰዎችን ከእርሱ ጋር የሚያስታርቅ ድኅነተ ነፍስ የሚያሰጥ አልነበረም። (ኢሳ 59÷16)
- በመጨረሻም የገዛ ክንዱን መድኃኒት አድርጎ ለዓለም ሰጠ፣ (ኢሳ 9÷6, ዮሐ 3÷16) ቅ/ኤፍሬም "ፈነወ ለነ መዝራዕቶ ልዑለ" እንዳለ።
- ዓለምን እንዲሁ ስለወደደ ልጁን ለዓለም ሰጠ (ኢሰ 9÷6, ዮሐ 3÷16)

## አዳኙ የእግዚአብሔር ልጅ እንዴት ተገለጠ?

- የተስፋው ቃል ጊዜው ሲደርስ ከድንግል ተወለደ (ገላ 4÷4)
- ሰዎች በኃጢአት ይወለዱ እንደነበር ያይደለ (ኢዮ 14÷4, 15÷14, መዝ 50÷5-6)
- ያለኃጢአት መንፈስ ቅዱስ ከኃጢአት በጠበቃት የእግዚአብሔር ጥበቃ ካልተለያት ድንግል ተወለደ፣ (ሉቃ 1÷26-37, ዕብ 2÷17)
- ከኃጢአት በቀር እንደእኛ ፍጹም ሰው ሆነ (ዕብ 4÷15)
- በየጥቂቱ አደገ፣ (ገላ 4፤2-5) ዓመታት የማይቆጠርለት ዕድሜው ሠለሳ ዓመት ሆነው ተባለ፤ (ሉቃ 3÷23)

- በአባቱም ፊት በሰውም ፊት ፍጹም ቅዱስ ነበር፣ (ሉቃ 2፥40)
- ጠላታችን ሰይጣን ሰው ሆኖ በተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ ላይ አለኝ የሚለው አጣ ማለት ምንም በደል አልተገኘበትም፣ (ዮሐ 14፥30)
- ሰዎችም ለክስ ምክንያት እስኪያጡ ድረስ ሁለተኛው አዳም ንጹሐ ባሕርይ ሆነ (ሉቃ 23፥13-17, ዮሐ 18፥38, 19፥1-20) መስቀል ሲሰቀል የሚጽፉት የዕዳ ደብዳቤ ጠፍቶ ስሙን ብቻ "ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ" ብለው እስኪጽፉ ድረስ ጻድቅ ሆኖ ተገለጠ።
- በቃሉ ፍጹም ሆኖ ተገለጠ (ኢሰ 53፥9, 1ኛ ጴጥ 2፥2-23)
- በመሆኑም አባቱ "የምወድህ ልጅ" (ማር 1፥11)፣ "ነፍሴ የወደደችው እጅግ ደስ የተሰኘችበት" (ኢሳ 42፥1-4) በማለት ከበደል በፊት የነበረውን አዳም መስሎ ልጁን ቢያየው "እጅግ መልካም ሆነ" (ዘፍ 3፥31) ብሎ የተናገረውን ደገመ። "ከአዕላፍ የተመረጠ" (መኃ 5፥10) ነበርና።

## አዳኙ ለምን ተገለጠ?

- የሰይጣንን ሥራ ሊያፈርስ ተገለጠ (1ኛ ዮሐ 3፥8)፣
- የጠፋውን ሊፈልግ የተጎዳውን ሊፈውስ (ሉቃ 19፥10)፣
- ሕይወት እንዲበዛልን ተገለጠ (ዮሐ 10፥10)፣
- ዲያብሎስን ከሥልጣኑ ሊሽር (ዕብ 2፥14-18)፣
- ኃጢአተኞችን ሊያድን (1ኛ ጢሞ 1፥15)፣
- ስለ እውነት ሊመሰክር (ዮሐ 18፥37)፣
- በሕግ በነቢያት በመዝሙራት ስለራሱ የተጻፈውን ሊፈጽም (ሉቃ 24፥44, ዮሐ 5፥46, ዮሐ 19፥30)፣
- ለድሆች ወንጌልን ሊሰብክ፣ ለታሠሩት መፈታትን፣ ለዕውሮች ማየትን፣ ለተጠቁት ነፃነትን፣ የጌታን ዓመት ሊሰብክ ተገለጠ (ሉቃ 4፥17-20, 43፥44)፣



- የዘለዓለም ሕይወትን ሊሰጠን ተገለጠ (ዮሐ 3፥16)፣
- ጽድቅ ሊሆነን ተገለጠ (ሮሜ 8፥1-2)

## አዳኙ ምን ሆኖ ተገለጠ?

- ሰው ሆኖ ተገለጠ (ዕብ 4፥15)፣
- የሕይወት ረሀብ ላጠቃቸው የሕይወት እንጀራ ሆኖ ተገለጠ (ዮሐ 6፥35-39)፣
- በኃጢአት ጨለማ ለሚመላለሱት ከመሰናክል ሊያድናቸው "ብርሃን" ሆኖ ተገለጠ (ዮሐ 8፥12)፣
- እረኛ ላጡ በጎች ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ መልካም እረኛ ሆኖ ተገለጠ (ዮሐ 10፥11, ሕዝ 34፥1-30)፣
- ሞት ላጠቃቸው ሞት ተስፋ ላስቆረጣቸው ትንሣኤና ሕይወት ሆኖ ተገለጠ (ዮሐ 11፥25)፣
- ወደ እግዚአብሔር መድረስ ላልሆነላቸው (ላቃታቸው) መንገድ ለጠፋባቸው "መንገድ" ይሆን ዘንድ ተገለጠ (ዮሐ 14፥6)፣
- እውነትን በሐሰት ለሚለውጡ "እውነት" ጎስቋላ ሰው ነኝ ማን ያድነኛል ለሚሉ "ሕይወት" ሆኖ ተገለጠ (ሮሜ 7፥24-25, ሮሜ 1፥18)፣
- የአንድነት የሦስትነት ምሥጢር ላልተገለጸላቸው ከሣቴ ኅቡዓት ሆኖ ተገለጠ (ዮሐ 14፥8)፣
- በእርሱ የሚገባ ሁሉ ይድን ዘንድ በር ሆኖ ተገለጠ (ዮሐ 10፥8)፣
- ጣፋጭ የወይን ግንድ ሆኖ ተገለጠ (ዮሐ 15፥1)

## ለመዳን በወልድ ማመን አለብን፤

"በልጁ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።" (ዮሐ 3፥36)፣

- "በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል" (ዮሐ 3፥18)፤
- "ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም። እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።" (ዮሐ 5፥24)፤
- "ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው? . . . በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።" (1ኛ ዮሐ 5፥1-15)፤
- "ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" (ዮሐ 1፥12)፤
- "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ።" (ዮሐ 16፥31)፤
- "ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔር ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ።" (ሮሜ 10፥9)፤
- "መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።" (ሐዋ 4፥12)

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸውን ሰው በአግባቡ ቢጠቀምባቸው ማለት በእግዚአብሔር ልጅ ቢያምን የሚከተሉትን ያገኛል።

- የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል። (ዮሐ 1፥12, 1ኛ ዮሐ 5፥2)
- ዓለምን ያሸንፋል። (1ኛ ዮሐ 5፥5)
- በነፍሱ ምስክር አለው (1ኛ ዮሐ 5፥10, ማቴ 10፥32)
- ሕይወት አለው (1ኛ ዮሐ 5፥13, ዮሐ 10፥10, ዮሐ 5፥24, ዮሐ 3፥3)



- አይፈረድበትም። (ዮሐ 3፥18, ዮሐ 5፥24)
- ይድናል። (ዮሐ 16፥31, 10፥9)
- አዲስ ፍጥረት ይሆናል። (2ቆሮ 5፥17, ኢሳ 43፥18-19)
- እግዚአብሔር በአዳም ኃጢአት ለሞተው አባቱ ይሆነዋል በልጁ በማመን ሁለተኛ ተወልዷልና (ሮሜ 8፥15, ገላ 4፥6)

## በልጁ የማያምን፤

- በልጁ የማያምን "ወልድየ አንተ" ብሎ የመሰከረውን አብን ሐሰተኛ ያደርጋል። (ማር 1፥11, 1ኛ ዮሐ 5፥9-11)
- አሁን ተፈርዶበታል። (ዮሐ 3፥18)
- የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይነዳል። (ዮሐ 3፥36)
- የላከውን አብን አያከብረውም (ዮሐ 5፥23-24)
- ዓለምንና የዓለም ገዥን አያሸንፍም (2ኛ ዮሐ 5፥5)

## *የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ሞተ፤*

- ሞት የኃጢአት ደመወዝ እንደሆነ ግልጽ ነው። (ሮሜ 6፥23) ኢየሱስ ግን የሞተው አንዳች ኃጢአት ሠርቶ ደመወዙን ለመቀበል አልነበረም፤ የሞተው በሰዎች ላይ የተፈረደውን የሞት ዕዳ የኃጢአት ደመወዝ ለመክፈል ነበር እንጂ።

ስለዚህ ማንኛውም ኃጢአተኛ ጌታ እንደሞተለት የእርሱን ዕዳ እንደከፈለለት ቢያምን ይድናል።

- ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፤ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሠጠ። ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ

ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ፤ እንደበጎች ትቅበዘበዙ ነበርና። (1ጴጥ1፥23-25)

- "ባየነውም ጊዜ እንወደው ዘንድ ደምግባት የለውም . . . በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንን ተሸከመ፣ ስለመተላለፋችን ቆሰለ . . . በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን፣ ነፍሱን ስለኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል።" (ኢሳ53፥2-12)
- "ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን ...ክብር ኃይል ይሁን" (ራዕይ 1፥6-7)
- "ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለኃጢአተኞች ሞቷልና።" (ሮሜ 5፥1)
- "...ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢአታችን ማስተስረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም።" (1ኛ ዮሐ 4፥10)

ሌሎችንም ጥቅሶች በማንበብ ስለእኛ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሞተ መረዳት ይቻላል። ማንም ሰው ስለ እርሱ ጌታ መሞቱን ካላመነ አይድንም ባለዕዳ ነውና።

## ሰው በክርስቶስ ሞት ለመጽደቅ ምን ማድረግ አለበት?

ማን ያድነኛል? ብሎ የጮኸ ሰው ከራሱ ተስፋ የለውም ሌላ መድኃኒት ለማግኘት አልቻለም። መዳን የሚችለው ጌታ እንደሞተለት በማመን እና እንዲሁም ለመስቀሉ ዋጋ ለደሙ የሚከፍለው ክፍያ ምንም ስለሌለው እምኖ የመስቀሉን ዋጋ በመቀበል መዳን አለበት። ይህን በሚመለከት ቅ/ጳውሎስ በሮሜ 3፥21 የጽድቅን መገኘት እንዲህ ይገልጸዋል። ቁ.21 "ያለ ሕግ" ቁ.22 "በማመን" ቁ.25 "እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ" ቁ.28 ያለ ሕግ ሥራ በእምነት ብሎ የሚመገነው እሴት የሌለው መሆኑን ይገልጻል። በክርስቶስ ያገኘው ጽድቅ ከሕግ ሥራ ውጭ ነው። (ቲቶ 3፥5) በተጨማሪ (ሮሜ 5፥16-18, ሮሜ 6፥23, ኤፌ. 2፥8) ይመልከቱ። ማንኛውም ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንና በመመላለስ ይጸድቃል። "እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው።" (ሮሜ 3፥22-26)

## ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእርሱ እንደሞተለት ባመነ ጊዜ የሚያገኘው ጥቅም፤

- ደሙ ከኃጢአት ያነጻዋል፣ "የልጁም ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።" (1ኛ ዮሐ 1፥7) ተብሎ እንደተጻፈ
- ደሙ ከቁጣው ያድነዋል፣ ". . . አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን።" (ሮሜ 5፥9)
- ኃጢአቱ ሁሉ ይቅር ይባልለታል። (ቆላ 2፥13, መዝ 102፥3)፣
- ኩነኔ የለበትም፣ "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም" (ሮሜ 8፥1-3)፣
- ሕይወት ይሰጠዋል። "ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን፤ በጸጋ ድናችኋልና . . . ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም።" (ኤፌ. 2፥5-8)፣
- ሰላም ይኖረዋል። "እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ" (ሮሜ 5፥1, ዮሐ 14፥27, 20፥19)፣
- የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ ወራሽ ይሆናል። "በዘለዓለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው።" (ቲቶ 3፥6-7)፣

- ከኃጢአቱ ይታጠባል፣ ይቀደሳል፣ ይጸድቃል፣"... ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፣ ጸድቃችኋል።" (1ኛ ቆሮ 6፥11)፣

ይህን መሰል ብዙ ጸጋዎችን ሰው ሊያገኝ የሚችለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው።

## ለመዳን የሚያስፈልጉ ሦስት ነገሮች

1. ጸጋ፤

ጸጋ ማለት የቸርነት ስጦታ፣ ያለ ሥራ የሚሰጥ፣ ያለ ዋጋ የሚቸር፣ ጥረታችን ሊያስገኝልን ያልቻለው መልካም ስጦታ፣ ነጻ ስጦታ ማለት ነው።

በሰው ልጅ ሕልውና ውስጥ ጸጋ ሰፊ ቦታ አለው እግዚአብሔር ለሰው (በጥንተ ተፈጥሮ) ብቁ አካልን በተፈጥሮ እንዲሁ ሰጠው ማንም ሰው ቢሆን በተፈጠረበት ጊዜ ቅርጹ ምን ዓይነት ሰው መሆን እንዳለበት ለእግዚአብሔር ሐሳብ የቸረ የለም። ሰው ከተፈጠረ በኋላ ኤደን ገነት ተሰጠችው (ዘፍ 2) ምቹ ቦታ የዕረፍት ቀን የተሰጠው ከእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር የሰጠውን ስጦታ በበደሉ ምክንያት ቢያጣም በጥንተ ተፈጥሮ በጸጋ የሰጠውን ስጦታ እንደሚሰጠው ተስፋ ሰጠው ክርስቶስ እስኪመጣ ኦሪት ጸጋ ሁና ተሰጠችው (1ኛ ዮሐ 1፥16, ገላ 3፥24) ሰው በሕግ በኩል መጽደቅ ቢያቅተው እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለዓለም ሰጠ።

"ሕጻን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና" (ኢሳ 9፥6) እግዚአብሔር ልጁን እንዲሰጥ አስቀድሞ ለእግዚአብሔር የተሰጠው ስጦታ ምንም አልነበረም። ለዚህ ነው ሐዋርያው ". . . ብድራቱን ይመልስ ዘንድ



ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው?" (ሮሜ 11፥35) ያለው ነገር ግን እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ዓለሙን እንዲሁ ስለወደደ ልጁን ሰጠን (ዮሐ 3፥16)። አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው "ፍቅር ሰሀቦ ለወልድ ኃያል እምመንበሩ ወአብጽሆ እስከ ለሞት" ትርጉሙም ኃያሉን ወልድን የሰው ልጅ ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው እስከሞትም አደረሰው እንዳለ። በፍቅሩ ሰው ሆኖ አዳነን እንጂ እርሱን ከሰማይ የምናወርድበት ጽድቅ አልነበረንም በጥንተ ተፈጥሮ ሰውን በአርዓያውና በአምሳሉ የሚፈጥርባትን መሬት በጸጋው አስጊጦ ፈጥሮ፣ ከእርሷም ቀዳማዊ አዳምን ብቁ አካልን ሰጥቶ እንደፈጠረው። በሐዲስ ተፈጥሮም እንዲሁ ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስን የሚነሳባት ገራሕተ ስሉስ ድንግል ማርያምን አስቀድሞ በጸጋው አስጊጦ ፈጠራት። ". . . በእርሱ ፊት ጸጋን አግኝተሻልና አትፍሪ" (ሉቃ 1፥30) "ረከብኪ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ኃደረ ላዕሌኪ" ጸጋን አገኘሽ መንፈስ ቅዱስ አደረብሽ ብሎ ቅ/ኤፍሬም እንደተናገረ።

ከእርሷም በተወለደው በኢየሱስ ክርቶስ ጸጋና እውነትን አገኘን (ዮሐ 1፥14) "ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ።" "እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና" (ዮሐ 1፥16) "ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ" (ዮሐ 1፥17) ልጁን የሰጠው በልጁ ለምናምን በጎውን ነገር ሊሰጠን ስለወሰነ ልጆቹ መሆን ለማንችለው የልጅነትን ሥልጣን ሊሰጠን ነው። (ዮሐ 1፥12) ሕይወትን ሰጠን፣ በጸጋው መዳንን ሰጠን (ኤፌ 2፥4-8) የተጠቀሱትን ሁሉ በሥራችን ሳይሆን በልጁ ስላመንን በበደላችን ሙታን ለነበርነው የእውነትን ሥራ መሥራት ላልቻልን እንዲሁ ሰጠን። በተጨማሪም "ያዳነን በቅዱስ አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና ይህም እንደራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደሥራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን" (2ኛ ጢሞ 2፥9)

ካለው ጋር ይስማማል። የእግዚአብሔር ጸጋ ምዕመናንን ያነጻል (የሐዋ 20፥32, 2ኛ ቆሮ 9፥14, 12፥9, 2ኛ ጢሞ 2፥1) መንፈሳዊ ስጦታዎችን እናገኝበታለን። (ሮሜ 12፥6-8, ኤፌ 3፥8) ይህ የጸጋ ስጦታ በክርስቶስ ደም የተገዛ ስለሆነ ቸል ልንለው አይገባም። ጸጋ እግዚአብሔር ለዓለም ድኅነት የተወሰነው የመጨረሻው የድኅነት ዕቅድ ነው። ወንጌልም ሕገ ጸጋ ናት። ከዚህ የተለየ ወንጌል የሚሰብክ የተረገመ ነው (ገላ 3፥ )። ከዚህ ላይ ትልቅ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር መዳናችን እኛ ለእርሱ የምንመገነው ነገር ባለመኖሩ በጸጋ ተሰጠ እንጂ በውድ ዋጋ ተገዝቷል። "እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ኑ፣ ገንዘብ የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም፣ ኑ ያለገንዘብም ያለዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ . . ." (ኢሳ 55፥1-3) "የተጠማም ይምጣ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ" (ራዕ 2፥17) እንደተባለ ሕይወትን ያገኘነው እርሱ ስለእኛ ቆስሎ ነው፣ ከሞት ያመለጥነው ስለእኛ ሞቶ ነው (ኢሳ 53፥3-12) የእግዚአብሔር ልጅ ለእኛ ሕይወት የሰጠን በጸጋ ይሁን እንጂ እኛን እና መዳናችንን እርሱ በክቡር ዋጋ ገዝቷል (1ኛ ጴጥ 1፥18-19, 1ኛ ቆሮ 6፥20)፤

## ጸጋ በኦርቶዶክሳውያን አባቶች ገለጻ የሚከተለውን ይመስላል፤

- ሐብተ ወልድና (የልጅነት ሀብት)
- ሕይወተ ልቡና (የልቡና ሕይወት)
- ገቢረ ተአምራት ወመንክራት (ድንቆችን ምልክቶችን ማድረግ መሥራት) ማር 16፥16-19
- ሥርየተ ኃጢአት (የኃጢአት ሥርየት ማግኘት ከኃጢአት ኃይል መዳን)
- ሐይው ከመ መላእክት (እንደ መላእክት ሕያው መሆን) (ማቴ.23፥30) ማለት ነው።



እነዚህ ሁሉ በጸጋው ይደረጋሉ ብለው ይተረጉማሉ። እውነቱም ይህ ነው "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን።" (2ኛ ቆሮ 13፥14)

## ጸጋ እግዚአብሔርን የምንቀበልባቸው መንገዶች

### 1.1 በጥምቀት፤

የማይታየውን ጸጋ እግዚአብሔር እናገኛለን፤ ለምሳሌ በጥምቀት ከምናገኛቸው ጥቂቶቹ፡-

- ዳግመኛ መወለድ (ዮሐ 3፥3-5, ቲቶ 3፥5, ዮሐ 1፥12)
- ሥርየተ ኃጢአት (የሐዋ 2፥38)
- ንጽሕናን ቅድስናን (1ኛ ጴጥ 3፥21, ኤፌ 5፥25-26)
- ለኃጢአት ሞተን ለእግዚአብሔር ፈቃድ መነሣትን። (ሮሜ 6፥3-10)
- ድኅነትን (ማር 16፥16, ዮሐ 3፥5)
- ወገንነትን የእግዚአብሔር ልጆች መሆንን (ገላ 3፥24-26)

### 1.2 በሜሮን (በመንፈስ ቅዱስ)

በአዲስ ሕይወት የማደግ ሥልጣን ይሰጠዋል። (1ኛ ዮሐ 2፥20-21, ኢሳ 11፥1) ላይ የተጠቀሱትን ስጦታዎች እንዲሁም ሮሜ 12፥4-8, ገላ 5፥22-24 የተጠቀሱትን ሐብታት እናገኛለን።

### 1.3 በንስሐ፤

የኃጢአትን ሥርየት ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅን እናገኛለን።

### 1.4 በሥጋ ወደሙ (በቅዱስ ቁርባን)

የማይታዩ ጸጋዎችን እንቀበላለን

- የኃጢአት ሥርየት እናገኛለን (ማቴ 26፥27-28)

- እኛ በክርስቶስ እንኖራለን፣ ክርስቶስም በእኛ ይኖራል (ዮሐ 6፥56, ዮሐ 6፥35-59)
- ክርስቲያኖች አንድ አካል እንሆናለን (1ኛ ቆሮ 10፥17)
- ስለ እርሱ ሕያው ሆነን እንኖራለን (ዮሐ 6፥53-57)
- የዘለዓለም ሕይወት እናገኛለን (ዮሐ 6፥54,57)

1.5 *በቀንዲል፤*

ከሥጋና ከነፍስ ደዌ እንፈወሳለን (ያዕ 5፥14-15)

1.6 *በተክሊል፤*

- ጋብቻችን ይባረካል (ዕብ 13፥3-4)
- እግዚአብሔር አንድ ያደርገናል (ማቴ 19፤ ተሰሎ 4፥3-4)

1.7 *ክህነት፤*

ለተጠራንለት አገልግሎት ብቁ የሚያደርግ የአገልግሎት ጸጋ ይሰጠናል (1ኛ ጢሞ 4፥14, 2ኛ ጢሞ 1፥6)

የማሠር የመፍታት ሥልጣን እንቀበላለን በጸጋውም እንድናለን።

2. እምነት (ሃይማኖት)

እምነት (ሃይማኖት) የሁሉ መሠረት ነው፤ ያለእምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም (ዕብ 11፥6) እዚህ ላይ ከእምነት ጸጋ የቀደመው እምነት ራሱ የጸጋ ስጦታ ስለሆነ ነው። ማንም ቢሆን እግዚአብሔር ስቦት፣ ራሱን ገልጦለት፣ በእርሱ ማመንን ሰጥቶት ካልሆነ በቀር በውስን አእምሮው እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ አጥንቶ



ስላላመነበት እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። የእግዚአብሔር ቃልም "የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል ማንም የለም" (ዮሐ 6፥44, 17፥6,24) ይላል።

"የመንፈስ ፍሬዎች . . . እምነት የውሃት . . ." (ገላ 5፥23) በማለት ይህንኑ አጽድቋል። እምነት የእግዚአብሔርን ጸጋ የምንቀበልበት ውስጣዊ እደ ልቡና (የልቡና እጅ) ነው፤ "እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ . . ." (ዕብ 4፥16) "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና" (ኤፌ 2፥8) በእምነታቸው እግዚአብሔርን ያስደሰቱትን እርሱም ስላመኑት ጸጋን ያበዛላቸውን የእምነት አርበኞች ታሪክ መመልከት ይጠቅመናል (ዕብ 11፥1-4) እምነት የዘለዓለም ሕይወትን ያሰጣል (ዮሐ 3፥16) እምነት ያጸድቀናል (ሮሜ 4፥3-5, ሮሜ 10፥9, ገላ 2፥16)

2.1 *የአጋንንት እምነት ከሰዎች እምነት ልዩ ነው፤*

- አጋንንት እግዚአብሔር እንዳለ ያምናሉ (ያዕ 2፥19)
- ኢየሱስንም ያውቃሉ ሲያስጨንቃቸውም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ይመሰክራሉ (ማቴ 8፥28-29, ማር 1፥23-28, 3፥11, 5፥1-7, ሉቃ 4፥33-37, ሉቃ 8፥28-29) ይህን ያህል ቢመሰክሩም ከእርሱ ጋር መኖርን ስለማይፈልጉ "ከአንተ ጋር ምን አለን" ይላሉ የሰዎች እምነት ግን ደስ የሚለውን ደስ የሚያሰኘውን በማድረግ ከእርሱ ጋር መኖርን ይፈልጋል። (ዮሐ 6፥66-69, ማር 5፥7-13)
- የአጋንንትና የተከታዮቹ እምነት የሞተ ነው (ያዕ 2፥19-26)።

እኛም "ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ" ብንል ፈቃዱን ካላደረግን እንነዳለን፣ እምነታችንም የአጋንንትና የተከታዮቹ እምነት ይሆንብናል።

## 3. መልካም ሥራ፤

እምነትን ያለመልካም ሥራ መግለጽ አይቻልም፤ (ያዕ 2፥18-21) ያለእምነትም መልካም ሥራ መሥራት አይቻልም። ማለትም መልካም ሥራ የማይሠራ አማኝ አይደለም። ያላመነም መልካም ሥራ አይኖረውም። በመሆኑም እምነት ያለሥራ የሞተ ሥራም ያለእምነት የሞተ ነው፤ (ያዕ 2፥18-26) አንድ ክርስቲያን መልካም ሥራ እንዲኖረው አስቀድሞ ከበረኃው ወይራ ተቆርጦ በመልካም ወይራ ላይ መዳቀል (መተከል) አለበት (ሮሜ 11፥24)። "ክፉ ዛፍ መልካም ማፍራት አይቻለውም ፍሬው መልካም ይሆን ዘንድ ዛፍዋን መልካም አድርጉ" (ማቴ 7፥20, 12፥33) ተብሎ እንደተጻፈ።

አንድ ሰው መልካም ሥራ ይኖረው ዘንድ ከመራራው ሥር ተነቅሎ ጣፋጭ ሥር ላይ መተከል አለበት። ማንኛውም ክርስቲያን ጣፋጭ ወይን ያፈራ ዘንድ በመልካሙ የወይን ሐረግ በክርስቶስ ላይ መኖር፣ የእርሱ ቅርንጫፍ መሆን አለበት። ከግንዱም መለየት የለበትም ካለእርሱ ምንም ማድረግ አይችልምና በእርሱ ላይ ሆኖ የማያፈራም ቢሆን ይወገዳል። "እውነተኛው የወይን ግንድ እኔ ነኝ . . . ፍሬ የማያፈራውም በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል . . . በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ፣ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፣ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም። እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፤ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል . . . " (ዮሐ 15፥17) አንድ ሰው ካላመነ ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ የእፉኝት ልጅ ነው (ማቴ 3፥7) የእፉኝትም ልጆች ክፉዎች ናቸው። ክፉዎች ደግሞ መልካም ማድረግ አይቻላቸውም ልብ ከአፍ የተረፈውን ስለሚናገር (ማቴ 12፥34) ከእሾህ ወይን ከኩርንችት በለስ አይለቀምም (ማቴ 7፥17) እንደዚሁ ከቀዳማዊ አዳም ልጆች



በመጀመሪያው አዳም ኃጢአት በተለከፉ ሁለተኛ ከዳግማዊ አዳም ካልተወለደ ሰው ሕይወት ውስጥ በጎ ነገር የለም በውስጡ ያለው ዘር የሰይጣን ነውና። (ሮሜ 7፥13-24) በጥንቃቄ ይመልከቱ።

ሁለተኛ ከእግዚአብሔር በመንፈስና በውኃ የተወለድን ግን የመንፈስ ፍሬ ልናፈራ (ገላ 5፥21-24) እግዚአብሔር እንድንመላለስበት ባዘጋጀልን መልካም ሥራ ልንጸና (ኤፌ 2፥10) ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ ግን እግዚአብሔር ቅጽራችንን ሊያፈርስ የአራዊት መናኸሪያ ሊያደርገን ይችላል (ኢሳ 5፥1-5) አጋንንት ሊሰለጥኑብን (ማቴ 12፥4-45, ራዕይ18፥1-6)፤ ከወይኑ አትክልት ውስጥ ቆርጦ ሊጥለን (ሉቃ 13፥6-9) ከቅድስቲቱ ከተማ ሊያባርረን (ራዕይ 22፥14-15) ይችላል።

ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች በውስጣችን ማን እንደሚኖር በመልካም ሥራችን እንግለጽ፣ መልካም ሥራችን ክርስቶስን ሊያስመስለን ስለሚችል (1ኛ ቆሮ 11፥1)፤ ስለመልካም ሥራችን ብቻ እንጸድቃለን ብለን እንዳናስብ ደግሞ መጠንቀቅ አለብን። ምክንያቱም ሰው ክርስቶስ ስለሱ ሞቶ መከራ ተቀብሎ ያዳነው እንደመሆኑ በሥራዬ እጸድቃለሁ ካለ የመስቀሉን ዋጋ መክፈል አለበት። ያን ለመክፈል ደግሞ ኃጢአተኛ ሰው አይችልም ሰው እንደ ሥራው ከሆነ በእግዚአብሔር መንግሥት መኖር ቀርቶ መድረኩን መርገጥም አይችልም። ነገር ግን ሰው እምነቱን በሥራ ሊገልጠው ይገባል፣ እምነቱን በሥራ የማይገልጽ ዓለማዊ ሰው ብቻ ነው ይህ ደግሞ አማኝ አይደለም። "ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው። ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል።" (1ኛ ዮሐ 4፥20)

## 5) የሰው መጨረሻው ምን ይሆናል?

የሰው መጨረሻው ያማረ ነው። ለሚያምኑ ሁሉ ደስ ያሰኛል፣ ለማያምኑ ደግሞ በጣም አሳዛኝ ነው። ምክንያቱም ሞት ኃጢአተኞችን ይጠብቃቸዋልና (ማቴ 25፥46, ራዕ 21፥8-9, ራዕይ 22፥14-15)

### የምዕመናን ዘለዓለማዊ ተስፋዎች

- የልቅሶና የመከራ ዘመን ያበቃላቸዋል (ራዕይ 7፥15-17, 21፥4)፣
- ባለመበስበስ፣ በክብር፣ በኃይል፣ በመንፈሳዊ አካል ተነሥተው ሞትን ይዘብቱበታል (1ኛ ቆሮ 15፥42-45)፣
- የመጣውን ጌታ ለመቀበል ወደሰማይ ይነጠቃሉ (1ኛ ተሰ 4፥16-17)፣
- ጌታቸውን ፊት ለፊት ያዩታል (1ኛ ቆሮ 13፥12, ራዕይ 1፥7, 22፥4)፣
- የሚያዩትን ጌታቸውን ወደመምሰል ይለወጣሉ (1ኛ ዮሐ 3፥2)፣
- መንግሥቱን ይወርሳሉ (ማቴ 25፥34)፣
- በቅድስና የጽድቅ ሥራ አጊጠው ወደ በጉ ሠርግ ይሄዳሉ (ራዕ19፥8-9)፣
- በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም በደስታ ይኖራሉ (ራዕይ 21፥2-3)፣
- ሽልማታቸውን ይቀበላሉ (ራዕይ 22፥12, ዳን 12፥3, 2ኛጢሞ 4፥2-3, 1ኛ ቆሮ 9፥25, 1ኛ ጴጥ 5፥4, ፊልጵ 4፥1, 1ኛ ተሰ 2፥19)፣
- በእጅ ባልተሠራ ቤት ውስጥ ይኖራሉ (2ኛ ቆሮ 5፥1-2, ዮሐ 14፥2-3)፣
- ሁሉም አዲስ ይሆንላቸዋል (ራዕ 21፥5)፣
- በግንባራቸው አዳኝ የሆነው ስሙ ይጻፍላቸዋል (ራዕ 22፥4, ራዕ 3፥12)፣
- እግዚአብሔር ለዘለዓለም አምላክና አባት ይሆንላቸዋል እነሱም ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ ሆነው ይኖራሉ (ራዕ 21፥3-7)፣
- ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይሆንም፣ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም ለዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይነግሣሉ (ራዕ 22፥5)።



| | |
|---|---|
| ወልድ ተብሎ ውሉደ እግዚአብሔር | (ሮሜ 8፥14-17) |
| ክርስቶስ ተብሎ ክርስቲያን | (የሐዋ 11፥26) |
| ነቢይ ተብሎ ነቢያት | (ዘዳ 18፥15-18, ሐዋ 13፥1) |
| ካህን ተብሎ ካህናት | (ዕብ 5፥6, ጴጥ 2፥9, ራዕ 1፥6-7) |
| ንጉሥ ተብሎ ነገሥታት | (ራዕ 19፥16, 20፥6) |
| ሐዋርያ ተብሎ ሐዋርያት | (ዕብ 3፥1, ሉቃ 6፥13) |
| ቅዱስ ተብሎ ቅዱሳን | (1ኛ ጴጥ 1፥15) |
| ጻድቅ ተብሎ ጻድቃን | (ዕብ 12፥23, ራዕይ 3፥14) |
| ምዕመን ተብሎ ምዕመናን | (ራዕይ 3፥14, ዕብ 2፥17) |
| ኀሩይ ተብሎ ኀሩያን | (ዕብ 8፥6, 1ኛ ጴጥ 1፥2) |
| መልአክ ተብሎ መላእክት | (ራዕይ 10፥2, ዕብ 2፥10) |
| ቡሩክ ተብሎ ቡሩካን | (ሉቃ 1፥42, ማቴ 25፥34) |

*እንዲህ ላሰኘን ለተሠዋው በግ ክብር ይሁን!*

*አሜን*

**ጥያቄዎች**

1. መዳን ምን ማለት ነው? በስንት ይከፈላል? እኛ ያገኘነው ምን ዓይነት መዳን ነው?
2. ሰው እንዴት ተፈጠረ?
3. በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ መፈጠር ማለት ምን ማለት ነው?
4. ሰው ከተፈጠረ በኋላ እንዴት ይኖር ነበር?
5. ሰው ለእንስሳት ስም ማውጣቱ ስንት ነገር ያስተምራል?
6. ሰው ዘለዓለማዊ ሆኖ ተፈጠረ ማለት ምን ማለት ነው?
7. በዚህ ትምህርት ውስጥ ሰው መድኃኒት የሚያስፈልገው ሐመምተኛ ነበርን?
8. ፈታኙ ማን ነበር? ስሞቹስ እነማን ናቸው? ትርጉማቸውስ?
9. ፈታኙ ለምን በነዚህ ስሞች ተጠራ?

10. ፈታኙ እንዴት ከሰማይ ወደ ምድር ተጣለ?
11. ፈታኙ ራሱን ወደ ሰው ያቀረበባቸው መንገዶች ስንት ናቸው? ምን ምን ነበሩ?
12. የሰው ውድቀት እንዴት ነበር?
13. ከውድቀት በኋላ የተከሰተው የመጀመሪያው አሳዛኝ ነገር ምን ነበር?
14. ከውድቀት በኋላ የተከሰቱት አሳዛኝ ነገሮች ስንት ነበሩ?
15. ሰው ከነዚህ ነገሮች ለመዳን የቻለበት ነገር ነበር ወይ? ለምን?
16. በሮሜ የተጠቀሰው ታሪክ ስለሰው ውስጣዊ ባህርይ (ንጽሐ ጠባይዕ) ምን ያስተምራል?
17. የሰው ልጅ ራሱን ለማዳን ያደረገው ሙከራ አልሳካለት ሲል ምን ብሎ ጮኸ?
18. የተስፋ ቃል ማለት ምን ማለት ነው?
19. በስንት መንገድ ተስፋውን እግዚአብሔር ተናገረ? በምን በምን?
20. የመጀመሪያዎቹ የተስፋ ቃላት ምን ምን ነበሩ? የት ላይ ተጠቅሷል?
21. በነቢያት ተነግረው ፍጻሜ ያገኙ ስንት የተስፋ ቃላት ከሐዲስ ኪዳን ጋር ተዛምደዋል?
22. ሰው ለምን በሕግ በኩል ለመዳን አልቻለም?
23. የሰው ደኅንነት ለምን በፍጡራን በኩል አልተፈጸመም? ለምሳሌ በሰዎች፣ በመላእክት፣ በዓለም ባለው ሀብት ሁሉ።
24. ሕግን መፈጸም ማለት ምን ማለት ነው?
25. የአዳኙ የእግዚአብሔር ልጅ መገለጥ እንዴት ነበር?
26. ለምን አዳኙ ተገለጠ?
27. አዳኙ ምን ሆኖ ተገለጠ?
28. በወልድ በማመን መዳን ማለት ምን ማለት ነው?
29. በወልድ የሚያምኑ ከሚያገኙዋቸው ጸጋዎች ጥቂቶቹን ይጥቀሱ?
30. በልጁ የማያምኑ ምን ዓይነት ፍርድ ይጠብቃቸዋል? ስንት ነጥብ ስለዚህ አነበቡ?



31. ክርስቶስ ስለሰው ሞተ ማለት ምን ማለት ነው?
32. ሰው በክርስቶስ ሞት ለመጽደቅ ምን ማድረግ አለበት?
33. ኃጢአተኛ ሰው ክርስቶስ እንደሞተለት ሲያምን ምን ያገኛል?
34. ሰው በክርስቶስ ባያምን ግን በጎ ሥራ ቢሠራ ለኃጢአቱ ዋጋ በጎ ሥራው ሊሆነው አይችልምን?
35. ጸጋ ምን ማለት ነው? የጸጋ መንገዶች ምን ምን ናቸው?
36. እምነት ምንድን ነው? የእኛ እምነት ከአጋንንት በምን ይለያል?
37. ከመልካም ሥራና ከእምነት ማን ይቀድማል?
38. መልካም ሥራ የምን መግለጫ ነው?
39. መልካም ባንሠራ በኢየሱስ ካመንን መዳን አንችልምን? ለምን?


መምህር ልዑለ ቃል አካሉ ዓለሙ
መ.ሣ.ቁ. 270
አዲስ አበባ
Leulekal Akalu Alemu
266 Robbin Street
Decatur G.A. 30030
U.S.A.